የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ማውጫ

መመሪያ ቁጥር 139/2018 ዓ/ም

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሣ እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ-----ገጽ

መግቢያ

መንግስት ለሕዝብ አገልግሎትለሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች መሬትን መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በፌዴራል እና በክልል መንግስታት ለሚከናዎኑ መሰረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ከሆነ ለባለይዞታዎች የሚከፍለው የንብረት ካሳ፤ የልማት ተነሺ ድጋፍ፤ የኢኮኖሚ ጉዳ ካሳ፤ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የስነ ልቦና ጉዳት ካሳ ወጪ የመክፈል ግዴታ የማን እንደሆነ መደንገግ በማስፈለጉ፣

የክልሉ ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉና የነዋሪዎቹም ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ በከተሞች ፕላን መሠረት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ ለመሠረተ ልማት፣ ለኢንቨስትመንትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል መሬትን መልሶ ማልማት አስፈላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም በገጠር ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች መሬት አዘጋጅቶ ማቅረብ በማስፈለጉ፤

የመሬት ይዞታ እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ተገቢና ተመጣጣኝ ካሣና የተነሺ ድጋፍ ለመክፈል ግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን መሠረታዊ መርሆዎችን ለይቶ መወሰን በማስፈለጉ እና ካሣውን የመተመን የመክፈል እና ተነሺወችን መልሶ የማቋቋም ሥልጠንና ኃላፊነት ያለባቸውን አካላት በግልፅ ለይቶ ለመወሰን በማስፈለጉ፣

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

ከይዞታ መነሳትና ካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ ስለሚኖር ይቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት በግልጽ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 26 ንኡስ አንቀጽ 2፣ በተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 1336/ 2017 እና ደንብ ቁጥር 472/2012 አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 1 እንዲሁም በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 88 ንዑስ አንቀፅ 1 ለክልሉ በተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣን መሰረት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሣ እና የልማት ተነሺዎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 139/20/18 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጎሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር፤

1. **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፡፡
2. "ሕገ መንግሥት" ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሕገ መንግሥት ነው፡፡
3. **"ክልላዊ መንግስት"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ማለት ነው፡፡
4. **"አዋጅ"**ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን፣ ካሣ የሚከፈልበትን እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 እና የተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 1336/2016 ነው፡
5. "ደንብ" ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬት ሲለቀቅ ስለሚከፈል ካሣ እና ተነሺዎችን ስለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 472/2012 ነው፡፡
6. **"ቢሮ"** ማለት የክልሉ የትራንፖርትና መንገድ ልማት ፤የከተማ መሠረት ልማት፤ ግብርና ቢሮ ነው፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

7. “ጽ/ቤት“ ማለት በዚህ መመሪያ የተገለፁ ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላትን ሥራ የሚያስተባብር ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ነው
8. **“የፌዴራል መንገድ“** ማለት የብሄራዊ መንገድ አውታር አካል ያልሆነ በክልሉ ውስጥ የሚገነባ ማለት ነው፤
9. **“የክልል መንገድ“** ማለት የብሄራዊ መንገድ አውታር አካል ያልሆነ በክልሉ ውስጥ የሚገነባ የገጠር መንገድ፣ የኮሚኒቲ መንገድ እና የመሳሰሉት ሌሎች ሲሆኑ በመንገዶች ክልል ውስጥ የሚገኙ ድልድዮች፣ ፋካዎች፣ የውሃ ማውረጃ ቦዮች፣ የትራፊክ ደህንነት ምልክቶችንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤
10. **“የኮሚኒቲ መንገድ“** ማለት በክልሉ መንግስት የመንገድ ፖሊሲ መሰረት የአካባቢው ህዝብ በገንዘቡ እና በጉልበቱ ወይም በእርዳታ የሚያሰራውና የሚጠግነው መንገድ ማለት ነው፤
11. **“የመንገድ ስራ“** ማለት የመንገድ ግንባት፣ የጥገና ማሻሻል ወይም መልሶ ግንባታ ሲሆን ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ይጨምራል፤
12. **“የህዝብ ጥቅም”** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማጎልበት የዞን ካቢኔ፣ ወይም አግባብ ባለው የክልሉ አካል በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በልማት ዕቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት ለሕዝብ የተሻለ የጋራ ጥቅምና ዕድገት ያመጣል ተብሎ የተወሰነው ነው ፡፡
13. **“የንብረት ካሣ”** ማለት የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለሚወሰንበት ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሰፈረው ንብረት ወይም ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ በዓይነት ወይም በገንዘብ ወይም በሁለቱም የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡
14. **“የልማት ተነሽ ካሣ”** ማለት ባለይዞታው የመሬት ይዞታውን ሲለቅ በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብቱ በመቋረጡ ምክንያት የሚደረሰን ጉዳት ለማካካስ የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡
15. **“የልማት ተንሺ ድጋፍ”** ማለት የመሬት ባለይዞታ ከመሬቱ በጊዜያዊም ሆነ በቋሚነት ሲነሳ ከአዲሱ አካባቢ ጋር መላመድ እንዲችል ከንብረት እና ከልማት ተነሺ ካሣ በተጨማሪ በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ ነው፡፡
16. **“የኢኮኖሚ ጉዳት ካሣ”** ማለት ከቦታቸው ያልተነሱ ነገር ግን መሬት ለሕዝብ ጥቅም በመለቀቁ ምክንያት በመቀጠር ወይም በመነገድ ወይም በማከራየት እና ከመሳሰሉት ያገኙት የነበረ ገቢ በመቋረጡ ለሚደረስ ጉዳት የሚከፈል ካሣ ነው፡፡
17. **“የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ሥነ“** ልቦና ጉዳት ካሣ” ማለት ለተነሺ ከነበረበት አካባቢ በመነሳቱ የነበረው ማህበራዊ ትስስር በመቋረጡ የሚከፈል የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የሥነ- ልቦና ጉዳት ማካካሻ ክፍያ ነው ፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

18. **"መልሶ ማቋቋም"** ማለት ለልማት ተብሎ በተወሰደው መሬት ምክንያት የሚያገኙት ጥቅም ለሚቋረጥባቸው ተነሺዎች ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው የሚሰጥ ድጋፍ ነው፡፡

19. **"ቀመር"** ማለት ለህዝብ ጥቅም በሚለቀቅ መሬት ላይ ለሠፈረ ንብረት ወጥ የሆነ የካሣ ስሌት የሚሰራበት ዘዴ ነው፡፡

20. **"ቋሚ ማሻሻያ"** ማለት በይዞታው ላይ የምንጣሮ ድልደላና እርከን ሥራ፣ ውሃ መከተር ሥራ እና የግቢ ንጣፍና ማስዋብ የመሳሰሉትን ሥራዎች ያጠቃልላል፡፡

21. **"የማቋቋሚያ ማዕቀፍ"** ማለት ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከመሬት ይዞታቸው እንዲነሱ ሲደረግ ዘላቂ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊኖራቸው የሚያስችል የሥራ መርሐ ግብር ነው፡፡

22. **"የወል ይዞታ"** ማለት ከመንግሥት ወይም ከግል ይዞታነት ውጭ የሚገኝና የአካባቢው ማህበረሰብ ለግጦሽ፣ ለደንና ለማህበራዊ አገልግሎት በጋራ የሚጠቀሙበት የመሬት ይዞታ ነው፡፡

23. **ሰብል"** ማለት በአንድ አዝመራ ወቅት የሚዘራ ወይም የሚተከል እና የሚሰበሰብ ማንኛውም እጽዋት ነው፤

24. **'የደረሰ ሰብል'** ማለት በመሬት ላይ ተዘርቶ ወይም ተተክሎ የሚገኝና ሊሰበሰብ የሚችል ሰብል ነው፤

25. **"ቋሚ ተክል"** ማለት ወቅቱን ጠብቆ ለዓመታት ምርት የሚሰጥ ተክል ነው፤

26. **"ቤት"** ማለት በገጠር ወይም በከተማ ለመኖሪያ፣ ለማምረቻ፣ ለንግድ፣ ለማህበራዊ ወይም ለሌላ አገልግሎት የተሰራ ወይም በመሠራት ላይ ያለ ማንኛውም ግንባታ ነው፡፡

27. **"ወቅታዊ የአካባቢ የገበያ ዋጋ"** ማለት ማንኛውም ንብረት በሚነሳበት ጊዜ ንብረቱ በሚገኝበት አካባቢ ባለው ገበያ ሊያወጣ ወይም ሊያስከፍል የሚችለው ዋጋ ነው፡፡

28. **"ቅድሚያ የማልማት መብት"** ማለት ለልማት በተፈለገ ቦታ ላይ በግል ወይም በጋራ ለቦታው በፀደቀው ዝርዝር የማስፈጸሚያ ፕላን መሰረት ለማልማት ቦታው ለሌላ አልሚ ከመሰጠቱ በፊት ለባለይዞታው የሚሰጥ የማልማት መብት ነው፡፡

29. **"የተመዘገበ ባለሙያ"** ማለት ስልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በዲዛይን ወይም በኮንስትራክሽን የባለሙያነት ወይም የአማካሪነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

30. **"ዝቅተኛ የቤት ደረጃ "** ማለት በክልል ወይም በከተሞች ፕላን መሠረት ለመኖሪያ የተፈቀደ አነስተኛው የቤት ደረጃ ነዉ፡፡

31. **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት በሕግ የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው

32. **"መሠረተ ልማት"** ማለት ከመሬት በላይ ወይም ከመሬት በታች ያለ መንገድ፣ የባቡር ሀዲድ፣ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የመስኖ የውኃ መስመር ወይም የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ግንባታዎችንም ይጨምራል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

33. **"የአግልግሎት መስመር"** ማለት ለህዝብ ጥቅም ስባል የሚለቀቅ መሬት ከመሬቱ በላይ ወይም ውስጥ የተዘረጋ የውኃ የፍሳሽ የኤሌክትሪክ ወይም የስልክ መስመር ሲሆን ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችንም ይጨምራል፡፡

34. **"ተነሺ"** ማለት ለሕዝብ ጥቅም መሬት በሚለቀቅበት ጊዜ በተለቀቀው መሬት ላይ ይኖር የነበሩ ባለይዞታ ነው፡

35. **"አቤቱታ ሰሚ"** ማለት በዚህ አዋጅ አፈፃፀም ላይ ለሚነሳ ቅሬታ የሚመለከት እና ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው፡፡

36. **"ይግባኝ ሰሚ"** ማለት አቤቱታ ሰሚ አካል የሰጠውን ውሳኔ በይግባኝ ተመልክቶ ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው

37. "እውቅና ያለው ገማች" ማለት ቋሚ ንብረቶችን ለመገመት አግባብ ባለው አካል እውቅና የተሰጠው ገማች አካል ነው፡፡

38. "አስቸኳይ ልማት" ማለት በመደበኛው ጊዜ መሄድ የማይችልና ለከፍተኛ ወጪ ሊዳርግ ወይም ከፍተኛ ገንዘብ ሊያሳጣ የሚችል መሆኑ ተረጋግጦ በመንግስት የተወሰነ የልማት አይነት ነው፡፡

39. "በቋሚነት የተወሰደ መሬት" ማለት ለተነሺው ተመላሽ የማይሆን ለህዝብ ጥቅም ተብሎ በቋሚነት ለልማት የተወሰደ መሬት ነው

40. "በጊዜያዊነት የተወሰደ መሬት" ማለት ለህዝብ ጥቅም ተብሎ በጊዜያዊነት ለመጠቀም የተወሰደ መሬት ሆኖ በውሉ መሰረት ለባለመብቱ የሚመለስ ይዞታ ነው

41. "ልዩድጋፍ" ማለት ለማልማት ጥያቄ ያቀረቡት ሴቶች ወይም አካል ጉዳተኞች ሲሆን ለማበረታታት ተብሎ የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ልዩ ድጋፍ ተደርጎላቸው የማልማት መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚደረግ ድጋፍ ነው፤

42. **"ውስብስብ መሰረት ልማት"** ማለት በተለመደው አሰራር የማይሰራ በአገር ውስጥ ባለው ባለሙያ ማይሰራ እቃዎችም በክምችት የማይያዝበት ከአገር ውጪ ግዥ የሚጠይቅ እና መሰረተ ልማት ተቋም ኃላፊ የፀደቀ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው የመሰረተ ልማት አይነት ነው፡፡

43. **"ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው ልማቶች"** ማለት ለሀገራዊና ለክልላዊ እድገትና ትራንፎርሜሽን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጡ የልማት ፕሮጀክቶች ወይም የትብብር መስኮችን ለማስፋት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሀገራቱ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ለሚኖራት የተሻለ ግንኙነት መሰረት እንዲጥሉ የታቀዱ ልማቶች ናቸው፡፡

44. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ፡፡

45. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

3. የመመሪያ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን ካሣ የሚከፈልበትንና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በዞን አስተዳደሮች፤ሪጂኦ ፖሊሲ ከተሞች፣ወረዳዎች፤ ከተማ አስተዳደሮች እና ቀበሌዎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

መሬት ለማስለቀቅ ስለሚፈፀም አሰራር መርሆችና ሥነ- ሥርዓት

4.መርሆዎች

1/ የመሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚደረገው በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ወይም በከተሞች መዋቅራዊ ዕቅድ ወይም በመሰረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት መሆን አለበት

2/ ለሕዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ የሚከፈል ካሳና የሚሰጥ የማቋቋሚያ ድጋፍ የተነሺዎችን የኑሮ ሁኔታ የሚያሻሽልና የሚያስቀጥል መሆን አለበት ፡፡

3/ በፌዴራልና በክልሉ መንግስት ለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች በአንድ አካባቢ ለሚገኙ ቦታዎች ለሠፈረ ንብረት እና ተጓዳኝ ጥቅም ማጣት የሚከፈል የካሳ ነጠላ ዋጋ ተመን ተመሳሳይ መሆን አለበት፡፡

4/ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ አሰራሩ ግልጽ አሳታፊ ፍትሃዊ እና ተጠያቂነትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

5. የሚለቀቀው መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ስለመወሰን

1/ አግባብ ያለው የክልሉ መንግስት፣ የዞን፣ ሪጂኦ ፖሊሲ ከተማ፣ የወረዳ ወይም የቀበሌ ካቢኔ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተሻለ ልማት ያመጣል ብሎ በመሬት አጠቃቀም እቅድ ወይም በልማት እቅድ ወይም በመሠረተ ልማት መሪ ፕላን መሠረት የሚለቀቀውን መሬት ለሕዝብ ጥቅም መሆኑን ይወሰናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፤ መሠረት ለመወሰን መሪ ፕላኑ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ፕላን ሊኖረው ይገባል፡፡

3/ ለሕዝብ ጥቅም መሬት አንዲለቀቅ ሲወሰን ለካሣ እና መልሶ ማቋቋም የሚያስፈልግ በጀትና በጀቱ እንደ ፕሮጀክቱ በማን እንደሚሸፈን አብሮ መወሰን አለበት ፡፡

4/ የመሬት ባለይዞታዎች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለፀው መስፈርት ሳይሟላ መሬታቸው ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ የሚሰጥ የሕዝብ ጥቅም ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም እንደ አስፈላጊነቱ የክልሉ ካቢኔ ለሕዝብ ጥቅም በሚል መሬት ማስለቀቅ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ለከተማ ወይም ለወረዳ አስተዳደሩ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡
፡

6. <u>መሬት የማስለቀቅ ሥልጣን</u>

በዚህ *መመሪያ* አንቀጽ 5 መሰረት ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ ውሳኔ የተሰጠበትን መሬት የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬቱ የማስለቀቅ እና የመረከብ ሥልጣን አለው፡፡

7.<u>ለባለይዞታዎች ቅድሚያ የማልማት መብት ስለመስጠት</u>

1/ በከተማ ለመልሶ ማልማት በተከለለ ቦታ ውስጥ ያለ ባለይዞታ በፕላኑ መሰረት ይዞታውን በግልም ሆነ በጋራ ቅድሚያ የማልማት መብት አለው፡፡

2/ የገጠር መሬት ባለይዞታ ለእርሻ ስራ የሚለቀቅ ሲሆን አቅሙ ካለው ይዞታውን በግልም ይሁን በቡድን በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መስረት ቅድሚያ የማልማት መብት አለው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀስ ፩ እና ፪ መሰረት ለተነሳ ቅድሚያ የማልማት መብት የሚጠበቅለት በፕላኑ መሰረት ለማልማት አቅም ማሳያ ማቅረብ ሲችል ነው ፡፡

4/ ቅድሚያ የማልማት መብት የሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታ እና አቅም ማሳያ መጠንና የጊዜ ገደብ በአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

5/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቅ ሆኖ ባለይዞታ ሆኖ ለማልማት ጥያቄ ያቀረቡት ሴቶች ወይም አካል ጉዳተኞች ሲሆን ለማበረታታት ተብሎ የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዉ፡፡

8. <u>መሬት የሚለቀቅበት ሥርዓት</u>

1/ የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ አስተዳደር መሬት ሲያስለቅቅ መከተል ያለበት ቅድመ ተከተል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

ሀ/ ተነሺዎች ከመነሳታቸው ቢያንስ ከስድስት ወር በፊት ስለልማቱ ዓይነት ፣ ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት በማወያየት እንዲያውቁት ማድረግ አለበት፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሰው ቢኖርም የሚመለከተው የክልል መንግስት ወይም የዞን አስተዳደር ሀገራዊ ወይም ክልላዊ ፋይዳ ላለው ለአስቸኳይ ልማት መሬት እንዲለቀቅ ከወሰነ ተንሺዎች ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ስለልማቱ አይነት ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደት በማወያየት እንዲያውቁት ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ/ እንዲለቀቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ከሚገኙ ተነሺዎች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች የባለመብትነት ማስረጃ እና ካሣ የሚከፈልባቸውን ንብረቶች የልኬትና የመጠን መረጃ መስብሰብ አለበት፡፡ ተነሺዎች ስለልማቱ እንዲያውቁት ከተደረገ በኃላ የተጨመሩ ማናቸውም ንብረቶች ካሳ አይከፈልባቸውም ፡፡

መ/በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ሐ” መሰረት የተሰበሰበውን መረጃ አጣርቶ ለልማት ተነሺ የሚሰጥ መብት ተጠቃሚነት ይወስናል፣ የካሣ መጠኑንም አስልቶ ካሳና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን ክፍያ ይከፈላል፡፡

ሠ/ ለሕዝብ ጥቅም እንዲለቀቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ለሚገኝ ተነሺ ወይም ሕጋዊ ወኪል የሚገባውን የካሣ መጠን እና/ወይም ምትክ ቦታ ስፈትና አከባቢን ወይም ቤት በመግለጽ በጽሁፍ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ መስጠት አለበት ፡፡

ረ/የሚለቀቀው ይዞታ የመንግስት ቤት የሰፈረበት ከሆነ የማስለቀቂያ ትዕዛዙ የሚደርሰው ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል ይሆናል፡፡

ሰ/ ተነሺን ከቦታው ማስነሳት የሚችለው ለተነሺው ካሣ ከተከፈለ እና ምትክ ቦታ ወይም ቤት ከተሰጠ በኂላ መሆን አለበት፡፡

ሸ/ መሬት የማስለቀቅ ስርዓት ዝርዝር አፈፃፀሙ በቢሮ በሚወጣ የአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

2/ ተነሺ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ባለመብትነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም ሠነድ በገጠርም ሆነ በከተማ መሬት የማስተዳደር በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል በሚያወጣው መርሐ-ግብር መሠረት ማቅረብ አለበት፡፡

3/ ተነሺው የካሳ ግምት በጹሁፍ እንዲያውቅ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ፡-

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

ሀ/በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ተገቢው ካሣ ካልተከፈለው በመሬቱ ላይ ከቋሚ ተክልና ግንባታ በስተቀር ሌሎች ሥራዎችን መስራት ይችላል፡፡

ለ/ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ተገቢው ካሣ ካልተከፈለው በመሬቱ ላይ ማንኛውንም በፕላን የሚፈቀድ እና ቀጣይ የቦታውን የልማት ወጪ በመንግስት ላይ የማያዛባ ሥራ መስራት ይችላል፡፡

ሐ/በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" መሰረት የተሰራ ሥራ ወይም የተደረገ ለውጥ በካሣ ስሌቱ ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት ፡፡

4/ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ ትዕዛዝ በደረሰው በ30(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ካሳ እና ምትክ ቦታ ወይም ቤት መውሰድ አለበት፡፡

5/ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በተቀመጠ ጊዜ ገደብ ውስጥ የካሣ ክፍያውን ካልወሰደ በከተማው ወይም በወረዳው አስተዳደር ስም በሚከፈት ዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥለት ይደረጋል፡፡

6/ ለባለይዞታ የሚሰጠው የመልቀቂያ የጊዜ ገደብ ካሣና ምትክ ቦታ ከተቀበለ ወይም ካሣው በዝግ ሂሳብ ከተቀመጠበት ቀን ጀምሮ ከ፩ሺ፲፭ (አንድ መቶ ሀያ) ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

7/ በሚለቀቀው መሬት ላይ ሰብል፣ ቋሚ ተክል ወይም ቋሚ የሆነ ሌላ ንብረት ከሌለ ባለይዞታው የልማት ተነሺ ካሣ ከተከፈለው በኃላ በ፴(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ይዞታውን ለከተማ ወይም ለወረዳ አስተዳደር ማስረከብ አለበት፡፡

8/ በሕገ ወጥ መንገድ በተያዘ ቦታ ላይ ለሰፈረ ንብረት ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ ለ30(ሰላሳ)ቀናት የሚቆይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወይም በቦታው በሰፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

9/ የማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ ወይም ባለንብረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያለ በቂ ምክንያት መሬቱን ካላስረከበ የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደሩ መሬቱን በራሱ ይረከባል፡፡ አስፈላጊም ሲሆን ለመረከብ የፖሊስ ኃይል ትብብር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

9. **<u>መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ኃላፊነት</u>**

1/ መሬት እንዲለቀቅለት የተወሰነለት አካል ለሥራው የሚፈለገውን መሬት መጠንና የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያሳይ ውሳኔ የተሰጠበት ማስረጃ ቢያንስ ሥራው ከመጀመሩ ከስድስት ወር በፊት ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ማቅረብ አለበት፡፡

2/ መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለውን ካሣ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ እንዲሸፍን ከተወሰነ ክልል እና ዞን የሚጠበቅበትን የገንዘብ ድርሻ ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ገንዘቡ ገቢ ተደርጎ ለተነሺዎች ካልተከፈለ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬት አያስለቅቅም፡፡

10. **<u>የአገልግሎት መስመሮች ስለሚነሱበት ሥርዓት</u>**

1/ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር በሚለቀቀው መሬት በላይ ወይም በታች የአገልግሎት መስመር መኖር አለመኖሩን የአገልግሎት መሥመር ባለቤት ለሆኑ ተቋማት ምላሽ እንዲሰጠበት በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ንብረት ካለው ለሚነሳው ንብረት ካሳ እውቅና ባለው ገለልተኛ ገማች በማስተመን ከነዝርዝር ማስረጃው ጥያቄው በደረሰው በ30(ሰላሳ) ቀን ውስጥ በጹሁፍ ለጠያቂው አካል ይላካል::

3/ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ግምቱ በደረሰው በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ለባለንብረቱ የንብረቱን ግምት ካሳ ይከፈላል፡፡

4/ የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈቀደለት በ ፮(ስልሳ) ቀናት ውስጥ ካሣ የተከፈለበትን የአገልግሎት መስመር አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት መስመሩ ባለቤት ክፍያው በተፈፀመ በ120 (አንድ መቶ ሃያ) ቀናት ውስጥ ውስብስብነት ያላቸውን የመሰረተ ልማት መስመሮች አጠናቆ ማንሳትና መሬቱን መልቀቅ አለበት፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

6/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 እና 5 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ካልተነሳ በአንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 9 መሰረት በማስነሳት ይዞታው የሚወሰድ ሲሆን በወቅቱ ተገቢውን ስራ ያልተወጣ የመሰረተ ልማት ተቋም ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

ክፍል ሦስት

የካሳ አወሳሰን፣ምትክ አሰጣጥ እና መልሶ ማቋቋም

11. ለሕዝብ ጥቅም መሬት ሲለቀቅ ለተነሺዎች ስለሚከፈል ካሣ

ለሕዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቀቅ ሲደረግ ለተነሺው ባለው የንብረትና የይዞታ መብት መሠረት የንብረት እና የልማት ተነሺ ካሣ ይከፈላል፡፡

12. የንብረት ካሣ

1/ የመሬት ይዞታን እንዲለቅ የሚደረግ ባለይዞታ በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እንዲሁም በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ ማሻሻያ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

2/ በሚለቀቀው የመሬት ይዞታ ላይ ለሰፈረው ንብረት የሚከፈል ካሣ ንብረቱን ለመተካት የሚያስችል ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚነሳው ቤት የሚከፈለው አነስተኛ የካሣ መጠን እንደየክልሉ፤ እንደ ዞኑ ተጨባጭ ሁኔታ ወይም ከተማ እና መሰረተ ልማት ቢሮ በሚያመጣው ስታንደርድ መሰረት ቢያንስ ዝቅተኛውን የቤት ደረጃ ሊያስገነባ የሚችል መሆን አለበት ፡፡

4/ በመሬት ይዞታው ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ የሚከፈል ካሣ በመሬቱ ላይ የዋለውን ገንዘብና የጉልበት ዋጋ የሚተካ ክፍያ በአከባቢው ወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ ይሆናል፡፡

5/ ንብረቱ ከሚገኝበት ስፍራ ወደ ሌላ አከባቢ ተዛውሮ እንደገና ሊተከልና አገልግሎት ለሚሰጥበት የሚችል ከሆነ የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ የሚሸፍን ካሳ መከፈል አለበት፡

6/ የተለያዩ ንብረቶች የሚሰሉበት የካሳ ቀመር እና ዝርዝር አፈፃፀማቸው በአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

13. ስለ የልማት ተነሽ ካሳ እና ምትክ ቦታ

1/ በቋሚነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ካሳ ምትክ ቦታ፡-

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

ሀ/ የመሬት ይዞታ በቋሚነት እንዲለቅ የሚደረግ የገጠር መሬት ባለ ይዞታ እንደአከባቢው ሁኔታ ከተወሰነበት መሬት ተመጣጣኝ ምርት የሚያስገኝ ምትክ መሬት የሚገኝ ሲሆን ምትክ መሬት ይሰጠዋል፡

ለ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሰረት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የሚሰጠው ከሆነ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን ከመለቀቁ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ካመረተው ሰብል የአከባቢ ዋጋ ተገምቶ ያገኘው ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ ታስቦ የልማት ተንሺ ድጋፍ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" መሠረት ተመጣጣኝ ምትክ መሬት የማይሰጠው ከሆነ መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ከመሬቱ ሲያገኝ የነበረውን ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ በአስር ዓመት ተባዝቶ የልማት ተነሽ ካሳ መከፈል አለበት፡

መ/ ከመኖሪያ ቦታው የሚነሳ ከሆነ ክልሉ፣ ዞኑ ወይም ከተማ አስተዳደሩ በሚያወጡት መመሪያ የሚወሰን ምትክ ቦታ እና የልማት ገነሽ ድጋፍ መከፈል አለበት፡፡

ሠ/ በጊዜያዊነት ለሚለቀቅ መሬት የሚከፈል የልማት ተነሽ ካሳ በማንኛውም ሁኔታ በዘላቂነት ከሚከፈል የልማት ተነሽ ድጋፍ መብለጥ የለበትም፡፡

ረ/ የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ በጊዜያዊነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሽ ድጋፍ ካሳ፡-

ሀ/ይዞታውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲለቅ ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱ ከመለቀቁ በፊት በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ ያገኘው ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ባለው ጊዜ ታስቦ የልማት ተንሽ ድጋፍ ካሣ ይከፈለዋል፡፡

ለ/በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ "ሀ" የሚከፈለው የልማት ተነሽ ካሣ መሬቱ የነበረውን ምርታማነት ለመመለስ የሚወሰደውን በአካባቢ የግብርና ተቋም የሚወሰን ተጨማሪ ጊዜ ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ/መሬቱ ተመልሶ በፊት ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት መስጠት የማይችል ከሆነ በቋሚነት እንደለቀቀ ተቆጥሮ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፤ መሰረት የልማት ተነሽ ካሳ ወይም ምትክ ቦታ ይሰጠዋል፡፡

መ/መሬቱ በጊዜያዊነት በተለቀቀበት የተከፈለ የልማት ተነሽ ካሳ በዚህ ንኡስ አንቀፅ ፊደል ተራ "ሐ" መሰረት በቋሚነት እንደለቀቀ ተቆጥሮ ከሚከፈል ካሳ ተቀንሶ ለተነሺው ልዩነት ይሰጠዋል፡፡

ሠ/ በጊዚያዊነት ለሚለቀቅ መሬት የሚከፈል የልማት ተነሺ ካሣ በማንኛውም ሁኔታ በዘላቂነት ከሚከፈል ለልማት ተነሺ ካሣ መብለጥ የለበትም፡፡

ረ/ የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን መመሪያ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ ስለወል ይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ

ሀ/ በቋሚነት ወይም በጊዚያዊነት ለሚለቀቅ የወል ይዞታ የልማት ተነሺ ካሳ አይከፈልበትም

ለ/ በወል መሬቱ ላይ የሚገኙ የግልና የወል ንብረት መለየት በመለየት የግል ንበረት ያለ እንደሆነ ካሳ ይከፈላል፡፡

4/ በቋሚነት ስለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ልማት ተነሺ ካሳ እና ምትክ ቦታ

የከተማ መሬት ባለይዞታ ከይዞታው በቋሚነት ተነሺ በሚሆንበት ጊዜ የሚከፍለው የልማት ተነሺ ካሳ እና የሚሰጠው ምትክ ቦታ በሚከተለው አግባብ ይሆናል፡-

ሀ/በቋሚነት የሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ ምትክ ቦታ ወይም መኖርያ ቤት እንዲያገኝ ይመቻቻል፡፡

ለ/የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከሆነ በቦታው ቤት እስኪገነባ ለሁለት አመት የሚኖርበት ቤት ያለክራይ ይሰጠዋል ወይም ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የሁለት አመት የልማት ተነሺ ካሳ ይከፈላል፡፡

ሐ/ የሚሰጠው ምትክ ቤት ከሆነ ለፈረሰበት ቤት በወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ የአንድ አመት የልማት ተነሺ ካሳ ይከፈለዋል፡፡

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ “ለ” እና “ሐ” የሚከፈል የልማት ተነሺ ካሳ መጠን ቢያንስ የአከባቢውን ዝቅተኛ የቤት ኪራይ ለመከራየት ከሚያስችል ያነሰ መሆን የለበትም፡፡

ሠ/ ተነሺዎች በነበሩበት አከባቢ ለነበራቸው የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና ለሚደርስ የስነ- ልቦና ጉዳት ማካካሻ ይከፈላቸዋል፡፡ መጠኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤

ረ/ የሚለቀቀው የሊዝ ይዞታ ከሆነ የሚሰጠው ምትክ ቦታ ከተለቀቀው መሬት በደረጃና በስፋት ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ ይህንን ለመፈፀም የማይቻል ከሆነ አማራጭ የአፈፃፀም ሁኔታ እንደየከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታ በአሰራር ሥርዓት የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሰ/ የምትክ ቦታ ወይም ቤት አሰጣጥ፣ የልማት ተነሽ ካሣ ቦታ እና ተያያዥ ጉዳዮች ዝርዝር አፈፃፀም ክልሉ፣ ዞኑ፣ **ሪጂኦ ፖሊሲ ከተማ** ወይም ከተማ አስተዳደሩ በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

5/ በጊዜያዊነት ስለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ የልማት ተነሺ ድጋፍ፡-

ሀ/ በጊዜያዊነት ለሚነሳ የከተማ ባለይዞታ ተነስቶ ለሚቆይበት ጊዜ ምትክ ቤት ወይም ወቅታዊ የኪራይ ግምት ተሰልቶ ተመጣጣኝ ቤት የሚከራይበት ክፍያ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ለ/ የከተማ ባለይዞታዎች በጊዜያዊነት በመነሳታቸው ምክንያት ላጡት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ካሳ ይከፈላቸዋል፡፡

ሐ/ የዚህ ንዑስ አንቀፅ ዝርዝር አፈፃፀም ክልሉ በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል፡፡

14. ገቢ በመቋረጡ ስለሚከፈል የኢኮኖሚ ጉዳት ካሳ

1/ ለህዝብ ጥቅም ተብሎ ቦታ እንዲለቀቅ ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ከይዞታው ሳይነሳ በጊዜያዊነት ወይም በዘለቃዊነት ሲያገኝ የነበረው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለተቋረጠበት ሰው የጉዳት ካሣ የሚከፍል ሲሆን ካሳው ስለሚገባው ተጎጂና የጉዳት ካሳው መጠንና አይነት ክልሉ በሚያወጣው የአሰራር ሥርዓት የሚወሰን ይሆናል ፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የካሳውን መጠንና አይነት ለመወሰን ከመቀጠል ከንግድ፣ ከኪራይ፣ ከእርሻ ውጪ መሬትን በመጠቀም የሚገኝ ገቢ እና የመሳሰሉ አመታዊ የተጣራ ገቢ ታሳቢ ሊያደርግ ይችላል፡፡

15. ከገጠር ወደ ከተማ ለተካለለ የከተማ አከባቢ ባለይዞታ የመኖርያ ቤት መስሪያ ቦታ ስለመወሰን

1/ ከገጠር ወደ ከተማ በተካለለ የአርሶ አደር ይዞታ ከመኖርያ ቤቱ ለሚነሳ ባለይዞታ በክልል፣ ዞን፣ በሪጂኦፖሊሲ ከተማ እና በከተማ አስተዳደር ካቢኔ የሚወሰን ሆኖ የከተማውን እስታንደርድ በመጠበቅ በ5 (ከአምስት መቶ) ሜትር ካሬ ያልበለጠ የመኖርያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለበት፡፡

2/ እድሜው 18 አመት እና በላይ ለሆነው የባለይዞታውን ገቢ በመጋራት አብሮ የሚኖር አርሶ ወይም አርብቶ አደር ልጅ የቦታ ስፋቱ የከተማውን አነስተኛ የመሬት ይዞታ ደረጃ የሆነ ለመኖርያ ቤት መስሪያ ቦታ መሰጠት አለበት ፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለመኖርያ የሚሰጠው ጠቅላላ የቦታ መጠን ከነበረው የመኖርያ ይዞታ በላይ መሆን የለበትም

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለፀው የመኖሪያ ይዞታ መጠን የባለይዞታ መኖሪያ ቤት ያረፈበትና አጥር ጊቢውን ይጨምራል ፡፡

16. <u>መልሶ ስለማቋቋም</u>

1/ የክልል መንግስት፣ ዞን፣በሪጂኦፖሊሲ ከተማ ፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ለካሳ ክፍያ እና ለመልሶ መቋቋምያ ፈንድ ያቋቁማል፣

2/ ክልል፣ ዞን፣ በሪጂኦፖሊሲ ከተማ ፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ተነሺዎችን በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስችል ማቋቋሚያ ማዕቀፍ የመቅረፅ ግዴታ አለባቸው ፡፡

3/ የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደር በተቀረጸው ማቋቋምያ ማዕቀፍና ለሚመደበው ማስፈፀምያ በጀት ተነሺዎችን የማቋቋም ግዴታ አለበት፡፡

4/ በገጠርም ሆነ በከተማ ለህዝብ ጥቅም መሬት የሚለቀቀው ለኢንቨስትመንት ከሆነ ተነሺዎች የክፍያ ስሌት በገጠር የአስራ አምስት ዓመት ሲሆን በከተማ ተግቢውን ካሳ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ካለተፈጸመ ተነሺዎች ከኢንቨስትመንቱ የሼር ባለቤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

5/ በገጠር ሆነ በከተማ የልማት ተነሺ በሼር ለመጠቀም ፍላጎት ኖሮት ባለሀብቱ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ሁኔታ ካለ ባለ ሀብቱ ለተነሺዎች አስቻይ ተለዋጭ መፍቴሄ ለተነሺው በባለሀብቱ እና በአስተዳደሩ መሰጠት አለበት ዝርዝሩ በአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

6/ የመልሶ ማቋቋምያ ማዕቀፍ ይዘትና ዝርዝር አፈፃፀም በአሰራር ሥርዓት ይወሰናል፡፡

17. <u>የካሳ ክፍያው ወጪ ተጋሪዎች እና ድርሻቸው</u>

መሬት ለህዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለው ካሳ እና መቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ በሚከተሉት አካላት ይሸፈናል፤

ሀ/ የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በፌደራል መንግስት ለሚከናወን መሰረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ከሆነ የልማት ስራው የሚካሄድበት ክልል፣ ዞን፣በሪጂኦፖሊሲ ከተማ ፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደር ለባለይዞታዎች የሚከፈለውን የንብረት ካሳ ፤የልማት ተነሺ ድጋፍ፤ የኢኮኖሚ ጉዳት ካሳ፤ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የስነ ልቦና ጉዳት ካሳ ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት

ለ/ በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር (ሀ) መሰረት ለሚከፈለው ካሳ የሚውለው ገንዘብ የሚመደበው ከክልል 40 በመቶ፣ ከዞን 25 በመቶ፣ ከወረዳ/ከተማ አስተዳደር 20 በመቶ እና ከማህበረሰብ በሚሰበሰብ 15 በመቶ ገቢ ይሆናል፤

ሐ) በዚህ አንቀፅ ሀ መሰረት በረጂዮ ፖሊሲ ከተሞች ለሚከፈለው ካሳ የሚውለው ገንዘብ የሚመደበው ከክልል 40 በመቶ፣ ከተማ አስተዳደሩ 40 በመቶ እና ከማህበረሰብ በሚሰበሰብ 20 በመቶ ገቢ ይሆናል፤

18. <u>ንብረት ስለመገመት</u>

1/ እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት ላይ ለሚገኝ ንብረት ካሳ የሚወጣውን ክልላዊ ቀመር መሰረት በማድረግ የግብርናና የደን ምርቶች በግብርና ቢሮ ባለሙያዎች እና የቤት ግምት በከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ ይገመታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የካሳውን መጠን የሚገምት ቢሮ ውክልና ከሰጠ የሚለቀቀው መሬት እንደሚገኝበት አከባቢ የሚመለከተው የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ተገቢውን ሙያ ያላቸው አባላት የያዘ ገማች ኮሚቴ በማቋቋም የሚገመት ይሆናል ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚቋቋመው ገማች ኮሜቴ ስራውን የሚያከናውንበት ክልሉ በሚያወጣው አሰራር ሥርዓት ይወሰናል ፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ቢኖርም የሚነሳው ንብረት የተለየ እውቀት የሚጠይቅ ሲሆን አግባብ ባለው የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ሊገምት ይችላል ፡፡

5/ የሚነሳው ንብረት የመንግስት መሰረተ ልማት ወይም የአገልግሎት መስመር ከሆነ የካሳ ግምቱ የሚዘጋጀው በንብረቱ ባለቤት ይሆናል ፡፡

6/ የካሳ ግምት የሚሰላበት ነጠላ ዋጋ ቢበዛ በየሁለት አመቱ መከለስ አለበት ፡፡

19_ . <u>የንብረት ግምት ሲሰራ የሚገኙ አካላት(ታዛቢዎች) በተመለከተ</u>

1<u>) ቤቶችን(ህ</u>ን<u>ፃዎችን) ሲሆን</u>

ሀ/ ባለንብረቱ (ተወካዩ) አንድ ሰው

ለ/ ቀበሌ ሊቀመንበር (የቀበሌ ም/ቤት አፈ ጉባኤ)

ሐ/ ከዞን ፣ከሪጂአፖሊሲ ከተማ፣ ከተማና መሰረተ ልማት የኮንስትራክሽን ዘርፍ ኃላፊ ፣

መ/ የማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅና የህንፃ ሹም

ሠ/ ሌሎች አራት ታዛቢዎች (በቀበሌ አቅራቢነት ሁለት እንዲሁም በባለንብረቱ አቅራብነት ሁለት ተሳታፊ ይሆናሉ)

ረ/ ግባብነት ያላቸው ሁለት የቴክኒክ ባለሙያ

2) <u>ግብርናና የግብርና ውጤቶች ሲሆን</u>

ሀ/ባለንብረቱ (ተወካዩ)

ለ/ ቀበሌ ሊቀመንበር (የቀበሌ ም/ቤት አፈ ጉባኤ)

ሐ/ ሶስት የግብርና ባለሙያ ከዞን፣ ከወረዳ እና ከቀበሌ

መ/ ሌሎች አራት ታዛቢዎች (በቀበሌ አቅራቢነት ሁለት እንዲሁም በባለንብረቱ አቅራብነት ሁለት ተሳታፊ ይሆናሉ)

<u>20. ምትክ ቦታ እና ካሳ የማይከፈልባቸው መሰረተ ልማት ግንባታዎች</u>

1/ በክልሉ መንገዶች ባለስልጣን የሚገነቡ መንገዶችና ድልድዮች

2/ በሁሉ አቀፍ የቀበሌ ተደራሽ መንገድ ፕሮጀክቶች የሚገነቡ መንገዶችና ድልድዮች

3/ በገጠር ተደራሽ የምግብ ዋስትና የሚገነቡ መሰረተ ልማቶች ይሆናሉ

4) ከላይ የተጠቀሰቅ ቢኖርም በድልድይ ግንባታ ቤት የሚፈርስ ከሆነ ወይም በመንገድ ግንባታ ምክንያት ጎርፍ የሚያፈናቅል ከሆነ ለተፈናቃይ በራሱ መሬት ወይም መሬት በማዘጋጀት ተመጣጣኝ ቤት ገንብቶ የመስጠት ሃላፊነት የወረዳው ውይም ከተማ አስተዳደሩ ይሆናል፡፡

21. አቤቱታ ሰሚ አካልና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ስለማቋቋም

1/ ዞን፣በሪጂኦፖሊሲ ከተማ ፣ ወረዳ/ከተማ አስተዳደሮች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቋቋም አለባቸው፡፡

2/ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ አካል እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አስፈላጊ ነው ብለው በወሰነባቸው ጉዳዮች ሊያቋቁሙ ይችላል፡፡

3/ የአቤቱታ ሰሚ አካል እና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

22. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>

1/ የመሬት ይዞታ ማስለቀቂያ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም እንዲለቅ ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ መብቱ ወይም ጥቅሜ ተነካብኝ የሚል ማንኛውም ተነሺ ትዕዛዙ በደረሰው በ30(ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለሚቋቋመው አቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው አካል የሚቀርብለትን አቤቱታ ከመረመረ በኃላ በ30(ሰላሳ)ቀናት ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከራካሪ ወገኖች በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

23. <u>ስለይግባኝ</u>

1/ በዚህ *መመሪያ* አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኝ ወገን አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሳኔው በፁሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ 30(በሰላሳ) ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘው ወገን ውሳኔው በጽሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30(ሰላሳ)ቀናት ለወረዳ ወይም ለከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውይም የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ከሆነ ልማቱ እንዳይጓተት ቦታውን አስረክቦ ክርክሩን የመቀጠል መብት አለው፡፡

3/ ተነሺው ንብረቱን በማስረከቡ እና በቅሬታ ምክንያት ካሳውን ባለመውሰዱ ለይግባኝ ክርክሩ የሚሆን በቂ ገንዘብ ከሌለውና በዚህ ምክንያት የሚቸገር ከሆነ መንግስት ነፃ የህግ አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ ነፃ የህግ አገልገሎት ለመጠቀም ፍቃደኛ ያለሆነ ተነሺ 50 በመቶ የካሳ ግምት ተቀብሎ ክርክሩን መቀጠል ይችላል፡፡

24. <u>አቤቱታ የቀረበበትን ቦታ ስለመረከብ</u>

1/ የመሬት ማስለቀቅ ትዕዛዝ የደረሰው ባለይዞታ በዚህ መመሪያ መሰረት አቤቱታ ያቀረበ ከሆነ የከተማውን ወይም የወረዳውን አስተዳደር ቦታውን መረከብ የሚችለው፡-

ሀ/ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት አቤቱታ አቅርቦ ውሳኔ ከፀና እና በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሳያቀርብ ሲቀር፣ወይም

ለ/ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ይግባኙን ሳይቀርብ ሲቀር ፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 ቢኖርም አቤቱታ የቀረበበትን ቦታ በህገ ወጥ መንገድ የተያዘ ቦታ ከሆነ በቦታው ላይ የሰፈሩ ንብረቶች በማውጣት የተሰራ ግንባታ እንዲፈርስ በማድረግ የከተማው ወይም የወረዳው አስተዳደር መሬቱን መረከብ ይችላል፡፡

ክፍል አራት

የሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ሥልጣንና ተግባር

25. የክልሉ ተቋማት ስልጣንና ተግባር

በሌላ ህግ ለቢሮው የተሰጠ ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ -

1/ የርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት

ሀ/ በሥራው የሚሳተፉና የሚመለከታቸውን አካላትን ያስተባብራል፣ያቀናጃል፣በበላይነት ይመራል

ለ/ የገማች ኮሚቴዎችን የሥራ ዕቅድ ይገመግማል፣ መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ሪፖርታቸውን ይቀበላል ከሚመለከተው አካላት ጋር ይገመግማል

ሐ/ የሥራ ሂደት የሚገጥሙ ችግሮችን ይፈታል፣ ባለድርሻ አካላትን ያቀናጃል፣ይከታተላል

መ/ የክልሉ መንግሥት የሚሰውን ሌሎች ተግባራትን ይፈጽማል

2/ የትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ

ሀ/ የመንገድ መሰረተ ልማትን በተመለከተ የከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ እና የግብርና ቢሮዎች ለልማት ተነሺዎች የካሳ ግመታ እንዲሰሩ ያስተባብራል፡፡

ለ/ የመንገድ መሰረተ ልማትን በተመለከተ ለተነሺዎች አስፈላጊው ካሳ እና የመልሶ ማቋቋም የተከፈለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሐ/ የመንገድ መሰረተ ልማትን በተመለከተ ከይገባኛል ነፃ ሆነው የቀረቡ ቦታዎችን ለይቶ ለልማቱ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

መ/ ለመንገድ መሰረተ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተቋማትን ያስተባብራል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

3/ የከተማና መሠረተ ልማት ቢሮ

ሀ/ ከተማን የሚመለከቱ የመመሪያ ድንጋጌዎች በከተሞች መከበራቸውን ይከታተላል ያረጋግጣል፡፡

ለ/ የከተማ ተነሺዎችን በማቋቋም ስራ ላይ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሐ/ የክልል፣ ዞን፣ ሪጂኦ ፖሊሲ ከተማ፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች መመሪያን ማስፋጸም እንዲችሉ ቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

መ/ መመሪያን ለማስፈጸም መመሪያዎችን በወቅቱ መውጣታቸውን ይከታተላል ይደግፍል፡፡

ሠ/ በከተማ ማልማት ምክንያት የተነሱ ባለይዞታዎች ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል ፣ለታዩ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፡፡

4/ <u>የግብርና ቢሮ</u>

ሀ/ የገጠር መሬትን የሚመለከት የመመሪያ ድንጋጌዎች በዞን፣ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

ለ/ የገጠር ተነሺዎችን በማቋቋም ስራ ላይ ድጋፍ ያደርጋል

ሐ/ በዞኖች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች መመሪያን ማስፈፀም እንዲችሉ የቴክኒክና አቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል ፡፡

26. <u>የዞኖች ወይም የሪጂኦፖሊሲ ከተሞች ስልጣንና ተግባር</u>

1/ ይህንን መመሪያና እና መመሪያን ለማስፈፀም የሚወጣውን አሠራር ሥርዓትመሠረት በወረዳና በከተማ አስተዳደሮች ወይም ከተሞች እንዲፈፀም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል ፡፡

2/ የመልሶ ማቋቋሚያ ማዕቀፍ ይቀርፃል፣ ይተገብራል ፡፡ ይህ ማዕቀፍ የሚተገብርና የሚመራ እራሱን የቻለ ተቋም ሊያቋቁም ይችላል፣ ወይም ካሉት ተቋሞች ይህንን ኃላፊነት የሚወጣ ይሰየማል፤

3/ ከተሞችና ወረዳዎች መመሪያን ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

4/ በልማት ምክንያት የተነሱ አካላት ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ጥናት ያካሄዳል፣ ለተለዩ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል፡፡

27. <u>የወረዳ እና የከተማ አስተዳደር ኃላፊነት</u>

1/ ተነሺዎች ለልማቱ አይነት ጠቀሜታና አጠቃላይ ሂደቱ ላይ ግልፅ ውይይት በማድረግ እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

2/ መሬት እንዲለቁ ለተደረጉ ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሣ ይከፍላል ወይም እንዲከፈል ያደርጋል፡፡

3/ የመልሶ ማቋቋምያ ማቀፍን ስራ ላይ ያውላል ፡፡

3/ ካሣ ተከፍሎበት እንዲለቀቅ በተወሰነ መሬት ላይ የሚገኘውን ንብረት በሚመለከት የተሟላ መረጃ ይይዛል፡፡

5/ ተነሺ አርሶ አደሮች ወይም አርብቶ አደሮች ወይም የከተማ ነዋሪዎች ኑሮአቸውን እንዲሻሻል የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ይሰራል ፡፡

6/ ተነሺዎችን የተመለከተ መረጃና ማስረጃ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

28. የቀበሌና የማህበረሰብ ኃላፊነት

ሀ/ ለልማቱ ቦታ ማዘጋጀት፣ መሬት ማቅረብና መስጠት

ለ/ ለልማቱ አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁስና ሌሎች ድጋፎን ማድረግ

ሐ/ ለልማቱ ተፈላጊ የሆኑትን አካላት እንዲሳተፉ ድርሻውን መወጣት

መ/ በወረዳ ወይም በኮሚቴ ሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፣ መፈጸም

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

29. ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ግዴታዎችን በህጉ አግባብና በወቅቱ ያልተገበረ ማንኛውም ግለሰብ፣ ተቋም እና የተቋም ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

30. የመሸጋገርያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመጽደቁ በፊት ክስ ቀርቦባቸው ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በቀድሞው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1161/2011 መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

31. መመሪያውን ስለማሻሻል

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

32. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ፡፡

33. **መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በመስተዳድር ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ 30 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ወላይታ ሶዶ

ታህሳስ 30 ቀን 2018 ዓ.ም

አቶ ጥላሁን ከበደ

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳደር

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

በ……ዞን/ ሪጂኦ ፖሊሲ ከተማ፣ወረዳ በ……..ከተማ

ህጋዊ የከተማ ቦታ ማረጋገጫ ያላቸው ባለመብቶች የምትክ ቦታ መቀበያ ሰርተፍኬት

ቁጥር……

ቀን……

ምትክ መሬት ተቀባዩ ስም……የባል/የሚስት ስም……

ክ/ከተማ……ቀበሌ…… መንደር……የቤት ቁጥር……የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ……ለልማት የተወሰደበት መሬት ስፋት…….ካ/ሜ፣የቦታው ደረጃ……፣ አገልግሎት……..፣ቦታው የተወሰደበት ጊዜ…….ዓ/ም፣የተወሰደበት ምክንያት……

……

.

ለልማት የተወሰደው መሬት አዋሰኞች፡-

በሰሜን……..…በደቡብ……..……በምሥራቅ……በምዕራብ……..……

ምትክ የተዘጋጀለት ቦታ አድራሻ

ክ/ከተማ……ቀበሌ……የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ……..…ስፋት…….ካ/ሜ፣ የቦታው አገልግሎት……. ደረጃ……

<u>ያዘጋጀው ባለሙያ</u>	<u>ያረጋገጠው</u>	<u>ያጸደቀው ኃላፊ</u>
ስም……	ስም……..	ስም……
ፊርማ……	ፊርማ……	ፊርማ…….
ቀን ……	ቀን ……..	ቀን ……...

SER BUREAU OF JUSICE (BOJ)

በ……ዞን/ሪጂኦ ፖሊሲ ከተማ/ ወረዳ በ……ከተማ

በከተማ ማስፋፊያ አካባቢ ህጋዊ መረጃ ያላቸው ባለመብቶች የምትክ ቦታ መቀበያ ሰርተፍኬት

ቁጥር……

ቀን……

ምትክ መሬት ተቀባዩ ስም …….. የባል/የሚስት ስም……ክ/ከተማ …… ቀበሌ…….. መንደር……የቤት ቁጥር……የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ…… ለልማት የተወሰደበት መሬት ስፋት…….ካ/ሜ፣የቦታው ደረጃ……፣ አገልግሎት……፣ቦታው የተወሰደበት ጊዜ …… ዓ/ም፣የተወሰደበት ምክንያት……

ለልማት የተወሰደው መሬት አዋሰኞች፡-

በሰሜን……..…በደቡብ……..……በምሥራቅ……በምዕራብ……..……

ምትክ የተዘጋጀለት ቦታ አድራሻ

ክ/ከተማ……ቀበሌ……የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ……..…ስፋት…….ካ/ሜ፣ የቦታው አገልግሎት……. ደረጃ……

<u>ያዘጋጀውባለሙያ</u>	<u>ያረጋገጠው</u>	<u>ያጸደቀው ኃላፊ</u>
ስም…….	ስም……..	ስም…….
ፊርማ…….	ፊርማ……	ፊርማ…….
ቀን ……..	ቀን ……..	ቀን ……..

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

በ……ዞን/ ሪጂኦ ፖሊሲ ከተማ/ወረዳ በ……ከተማ

በከተማ ማስፋፊያ አካባቢ ህጋዊ ማስረጃ ያላቸው ባለመብቶች ልጆች የምትክ ቦታ መቀበያ ሰርተፍኬት

ቁጥር……

ቀን……

ምትክ መሬት ተቀባዩ የአባት ስም……የእናት ስም……ምትክ መሬት ተቀባይ ልጅ ስም……ክ/ከተማ……ቀበሌ……መንደር……የአባቱ የቤት ቁጥር……፣ የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ……ከአባቱ ለልማት የተወሰደበት መሬት ስፋት…….ካ/ሜ፣የቦታው ደረጃ…….፣አገልግሎት……፣ቦታው ከአባቱ የተወሰደበት ጊዜ…….ዓ/ም፣የተወሰደበት ምክንያት……..

……

ለልማት የተወሰደው መሬት አዋሰኞች፡-

በሰሜን……..…በደቡብ…….……በምሥራቅ……በምዕራብ……

ምትክ የተዘጋጀለት ቦታ አድራሻ

ክ/ከተማ……ቀበሌ……የሰፈሩ ልዩ መጠሪያ……..…ስፋት…….ካ/ሜ፣የቦታው አገልግሎት……. ደረጃ……

ያዘጋጀው ባለሙያ	ያረጋገጠው	ያጸደቀው ኃላፊ
ስም……	ስም……..	ስም……..
ፊርማ……	ፊርማ……	ፊርማ……
ቀን ……	ቀን ……	ቀን ……

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

የልማት ተነሺ የሚከፈለው የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና የስነ-ልቦና ጉዳት ካሣ

ተ.ቁ.	የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና የስነ-ልቦና ጉዳት ካሣ ክፍያ	የማህበራዊ ትስስር መቋረጥና የስነ-ልቦና ጉዳት ካሣ ክፍያ መጠን ቦታው ላይ በኖሩበት አመትምህረት መጠን															
		ከ36 አመት በላይለተያዘ መሬት	ከ33-35 አመትለተያዘ	ከ21-30 አመትለተያዘ መሬት	ከ11-20 አመት ለተያዘ መሬት	እስከ10 አመት ለተያዘ መሬት											ምር መራ
1	ለማህበራዊ ትስስር መቋረጥ የሚከፈል ካሳ	27500 ሺ.ህ ብር	25000-27000	20000-24500	15000-19500	ከ10000 እስከ14500ሺ.ህ ብር											
2	የስነ-ልቦና ጉዳት ካሣ	32500 ሺ.ህ ብር	30000-32000	25000,29500	20 000-24500	ከ15 ሺ.ህ ብር እስከ 19500 ብር											
ጠቅላላ ድምር		60 ሺ.ህ ብር	59ሺ.ህ እስከ55 ብር	54ሺ.ህ እስከ45 ብር	44ሺ.ህ እስከ35 ብር	34 ሺ.	33 ሺ.	32 ሺ.	31 ሺ.	30 ሺ.	29 ሺ.	28 ሺ.	27 ሺ.	26 ሺ.	25 ሺ.		
		36 አመት በላይ	ከ35-31አመት	ከ30-21አመት	ከ20-11 አመት	10 አመት	9 አመት	8አመት	7አመት	6አመት	5አመት	4አመት	3አመት	2አመት	1 አመት		

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

SER BUREAU OF JUSICE(BOJ)

SER BUREAU OF JUSICE